# የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ፌዴሬላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) ሕገ መንግሥት ውስጥ ያላቸው ቦታ

በኢብራሂም ኢድሪስ*

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(4) "በኢትዮጵያ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሁሉ የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው" በማለት ይደነግጋል፡፡ ዓለም አቀግ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ልዩ ዓይነት የሆኑ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች[1] ናቸው፡፡ እስከ አሁን ድረስ፥ ኢትዮጵያ ዋና ዋና የተባሉትን የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን አጽድቃለች ወይም ተቀብላለች፡፡ እነዚህም እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተደገጉትን ሁለት የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችንና እንዲሁም በዓለም የሥራ ድርጅት፥ የስደተኞች ድርጅትና የትምህርት፥ የሳይንስና የባህል ድርጅት በመሰሉ የተባበሩት መንግሥታት ቅርንጫፍ ድርጅቶች የቀረቡ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ. በ1998 ዓ.ም. ኢትዮጵያ የአፍሪካን የሰዎችና ሕዝቦች መብቶችን ቻርተር አጽድቃለች፡፡

የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ እንዲፀድቁ የማድረግ አስፈላጊነት ሕገ መንግሥታዊ ባሕሪ ያላቸው ብዙ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያስችለናል፡፡ እነዚህም በተለይ የሚከተሉትን ሁለት የተለዩ ጉዳዮች ይመለከታሉ፡፡ የጸደቀ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ሳይወጣ የኢትዮጵያ ሕግ አካል እንደሆነ ተቆጥሮ በሀገሪቱ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል? እንደዚህ ያለው ስምምነት የኢትዮጵያ ሕግ አካል ከሆነስ በሀገሪቱ የሕግ ሥርዓት ደረጃ ውስጥ ከምን ቦታ ላይ ነው የሚገኘው?

በዓለም አቀፍ ሕግ ፍልስፍና ውስጥ እነዚህና እነዚህን የመሰሉ ጥያቄዎች ዓለም አቀፍ ሕግ ከብሔራዊ ሕግ ጋር ከሚኖሩት ግንኙነቶች አኳያ ዓለም አቀፍ እውቅናን ካገኙ ከሁለት አቅጣጫዎች ማለትም ከአሀዳዊና ከመንታ የአመለካከት መንገዶች

---

* ረዳት ፕሮፌሰር፥ ሕግ ፋክልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (የቀድሞ የሕግ ፋክልቲ ዲን)፡፡

[1] በዓለም አቀፍ ሕግ ውስጥ "Treaty," "Convention," "Pact," "Agreement," "Arrangement" እንዲሁም "Protocol" በሚሉት ቃላት መካከል ያልተስተካከለ አጠቃቀም አለ፡፡ ሁሉም ቃላቶች የሚያመለክቱት ሀገሮች ያደረጉዋቸውን ስምምነቶችና እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ሕጎችና ከሕገ መንግሥታቸው አንፃር በእነዚህ ስምምነቶች ለመገዛት የተስማሙበትን ሂደት ነው፡፡ የቃላቶቹ አመራረጥ የሚመራው በየሀገሮቹ እሳቤ ስለሆነ አንድ ወጥ የሆነ የስያሜ ሚዛን የላቸውም፡፡ ከእነዚህ ቃላቶች ውስጥ "Convention"ንና "Treaty" አንድ ላይ እና በመቀያየር ያገለግላሉ፡፡ ፀሐፊውም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ሁለቱን ቃላት በዚህ መልኩ መጠቀምን መርጧል፡፡

ሊተነተኑ ይችላሉ::[2] ይሁን እንጂ: እነዚህ የአመለካከት መንገዶች በባህሪያቸው ቲዎሪዎች በመሆናቸውና የሕግ ሊቃውንትንም ወደማያልቅ ክርክር የሚወስዱ በመሆናቸው የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በእነሱ ላይ ትንተና አያደርግም:: በምትኩም ተግባራዊነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የምርምር ትኩረቱን ለማድረግ ይሞክራል::

ነገሮች አሁን በሚገኙበት ሁኔታ፣ ከኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አኳያ ሲታዩ፣ ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚኖራቸው አፈጻጸምና በሀገሪቱ ሕጎች ደረጃም ውስጥ ያላቸውን ቦታ በተመለከተ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ቀጥተኛ መልሶችን ለመስጠት መሞከር አስቸጋሪ ነው:: ይህም በሦስት የተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል:: አንደኛው: የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ግልጽ ባለመሆናቸው ለጥያቄዎቹ ቀጥተኛ መልስ ለማግኘት አይቻልም:: ሁለተኛ፣ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን የሚመለከቱትን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች ለማብራራት የሚያስችል የዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት አዋጅ በፌዴራል ኢትዮጵያ ገና አልወጣም:: እንዲሁም ሶሥተኛው: ሁለተኛው የሕዝብ ምክር ቤት አካል የሆነውና ሥልጣኑም ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን መተርጎምን የሚያካትተው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚመለከቱ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎችን አተረጓጎም በተመለከተ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ አግባብነት ያላቸው ውሳኔዎች ገና አልወሰነም::

ይህንን አጭር ጽሑፍ ለመጻፍ ያስፈለገበትም ዋና ዓላማ፣ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሂደትና እንዲሁም እነዚሁ ስምምነቶች በሀገሪቱ የሕግ ሥርዓት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ለመመርመር ነው:: ይህንን ከግብ ለማድረስ አግባብነት ያላቸው የሕገ መንግሥቱና ሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች በቅርብ ይመረመራሉ:: በተጨማሪም፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ትኩረት በተደረገባቸው ጉዳዮች ላይ ብርሃን ለመፈንጠቅ ይቻል ዘንድ አግባብነት ያላቸውን የሌሎች ሀገሮች ሕጎችና ልምዶች ለመዳሰስ ተሞክሯል:: አስፈላጊ በሆነበት ቦታ የዓለም አቀፍ ሕግ ደንቦችና መርሆዎች እንዲሁ ተጠቅሰዋል:: በጸሐፊው አመለካከት ከጽሑፉ የሚገኘው ልምድ በኢትዮጵያ ውስጥ ለዓለም አቀፋዊ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ግንዛቤ ዕድገትና አፈጻጸም አስፈላጊነቱ የማያጠራጥረው የምሁራን የጋራ ጥረት ይጎለብት ዘንድ በእነዚሁ ምሁራን መካከል ጠለቅ ያለ ውይይት እንዲጀምር ለማነሳሳት ነው::

## I. ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ታሪካዊ ዕድገት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ፣ በጣም ቆየት ካለ ጊዜ ጀምሮ የሁለትዮሽ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አባል ሆና ቆይታለች:: በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የነበሩ የተለያዩ አካባቢያዊ መንግሥታት የሁለትዮሽ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተዋዋይ ሆነው ነበር:: ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹ፣ እ.ኤ.አ. በ1841 ዓ.ም. በእንግሊዝና በሸዋ፥ በ1843

[2] ማርክ ደብሊው ጄንስ፣ ሪቻርድ ኤስ ኬ እና አንቶኒ ደብሊው ብራድሊ፣ የአውሮፓ ሰብዓዊ መብቶች ሕግ፣ 1995፣ ገጽ 448::

ዓ.ም. በፈረንሳይና በሸዋ፥ በ1849 ዓ.ም. በሮላንድና በውቤ፥ በ1849 ዓ.ም. በፕላውደንና በአሊ እና በ1859 ዓ.ም. በራስልና በንጉሤ መካከል የተፈረሙ የጋራ ስምምነቶች ነበሩ።[3]

ነገር ግን፥ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብትና ሰብዓዊነት ሕግ ስምምነቶች መስክ መሳተፍ የጀመረችበት ጊዜ በቀድሞው የመንግሥታት ማህበር ውስጥ በአባልነት ከተመዘገበችበት እ.ኤ.አ. ከመስከረም 23 ቀን 1923 ዓ.ም.[4] ጀምሮ ነበር። በዚሁ ማህበር አባልነቷም ኢትዮጵያ ብዙ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብትና ሰብዓዊነት ስምምነቶችን ማጽደቋ የሚታወስ ነው። ለምሳሌ የባርነትን ተግባር የሚከለክለውን ስምምነት እ.ኤ.አ. በመስከረም 25 ቀን 1926 ዓ.ም. እና በጦር ሜዳዎች ውስጥ የቆሰለኞችንና የህመምተኞችን ሁኔታዎች ለማሻሻል ወጥቶ የነበረውን የጄኔቫ ስምምነት እ.ኤ.አ. በጥር 15 ቀን 1936 ዓ.ም. አጽድቃለች። እንዲሁም ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉን የሥራ ማህበር ልዩ ልዩ ስምምነቶች አጽድቃለች ወይም ተቀብላለች።

በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ዕድገት ውስጥ የኢትዮጵያ ሚና አዲስ ምዕራፍ መያዝ የጀመረውም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በጥቅምት 24 ቀን 1945 ዓ.ም. እንደተመሠረተ ነው። የደምባርቶን ኦክ ሀሳቦች እየተባለ በሚታወቀው የተባበሩት መንግሥታት ረቂቅ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ ለመምከር በዩናይትድ ስቴትስ ጥሪ ከተደረገላቸው 46 ሀገሮች ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን እ.ኤ.አ. በጥቅምት 24 ቀን 1945 ዓ.ም. ለማቋቋም በተጠራውም ስብሰባ ላይ ተካፋይ ነበረች።

እንዲሁም ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. የታህሣሥ 10 ቀን 1948ቱን ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጠቃሚ ሚና ከተጫወቱት ሀገሮች መካከል አንዷ ነበረች። የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ለዘመናዊው የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግ መሠረት ነው። ድንጋጌው ሲዘጋጅ አስገዳጅነት እንዳለው ሰነድ ያልተቆጠረ ቢሆንም በመግቢያው ውስጥ እንደተገለጸው ድንጋጌው የሁሉም ሕዝቦችና ሀገሮች ዋና የጋራ ክንውን ግንዛቤ ተወስዷል። ስለዚህም ድንጋጌው ቀደም ከአለው ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕግ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የድንጋጌው ተጽዕኖ በጣም ጉልቶ ከታየባቸው የኢትዮጵያ ሕጎች መካከል እ.ኤ.አ. በ1955 ዓ.ም. የተደነገገው የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ነበር። በወቅቱ ድንጋጌው የኢትዮጵያ ሕግ አካል ያልተደረገ ቢሆንም፥ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት አርቃቂዎች የሕገ መንግሥቱን የሰብዓዊ መብትና ነፃነት ድንጋጌዎችን ለመቅረጽ እንደዋነኛ ምንጭ ያደረጉት ድንጋጌውን ነበር።[5] በግምት እ.ኤ.አ. ከ1950ዎቹ እስከ 1960ዎቹ ድረስ ተከናውኖ በነበረው ሕጎችን በመጽሐፍ ወይም ኮድ መልክ የማዘጋጀት ሂደት፥ የኢትዮጵያ ሕጎች ዕድገት፤ በተለይም እ.ኤ.አ. የ1957 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፥ የ1961 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ እና የ1960 ዓ.ም. የፍትሐ ብሔር ሕግ በድንጋጌው ከፍተኛ ተጽዕኖ ሥር ለመሆን በቅተዋል። ከዚህም በላይ ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1957 ዓ.ም. በተደነገገው የኢትዮጵያ

---

[3] በኩረ ኅሩይ፤ ስለ ስምምነቶች ሕግ መግቢያ፥ የኢትዮጵያ ልማድ፥ ከ1841-1908፥ መመሪቂያ ጽሑፍ፥ የሕግ ፋክልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥1980፥ ገፅ 62-114 (ያልታተመ)።

[4] ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስን ስምምነት የፈረመችው በታህሣሥ 16 ቀን 1923 ዓ.ም. ሲሆን ያፀደቀችው ደግሞ በመስከረም 27 ቀን 1923 ዓ.ም. ነው።

[5] ጀምስ ሲ. ኤን ፖል እና ክርስቶፈር ክላፋም፥ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥታዊ እድገት፥ 1971፥ ገጽ 912-913።

ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ በተለይ የተካተቱት አንቀጽ 281 እና 282 እንደ ቅደም ተከተላቸው የተወሰዱት የዘር ማጥፋትን ከሚመለከተው የዓለም አቀፍ ስምምነትና እ.ኤ.አ. ነሐሴ 12 ቀን 1949 ዓ.ም. ከተደነገጉት አራቱ የጀኔቫ ስምምነቶች ነበር:: ኢትዮጵያ ስለዘር ማጥፋት የሚመለከተው ስምምነትና የአራቱ የጀኔቫ ስምምነቶች አባል የሆነችው ገና ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ነበር:: እስከ አሁን ድረስ፥ ኢትዮጵያ ዋና ዋና የተባሉትን የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን አጽድቃለች ወይም ተቀብላለች:: እንዲሁም፣ እ.ኤ.አ. በ1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ መብት ድንጋጌን እ.ኤ.አ. ሰኔ 1991 ዓ.ም. የሀገሪቱ ሕግ አካል እንዲሆን በግልጽ ማጽደቋ የሚያስደንቅ ነው:: ይህም የተከናወነው በሽግግሩ መንግሥት ቻርተር አማካይነት ነበር::[6]

የቀድሞዎቹን ሦስት የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥቶች (ማለትም እ.ኤ.አ. የ1931 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት፥ የ1955 ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ መንግሥትና የ1987 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት) በሚመረመሩበት ጊዜ ማንም በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችለው ጉዳይ ሁሉም ሕገ መንግሥቶች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የነበራቸው መሆኑን ነው:::: ከእነዚህም ሕገ መንግሥቶች መካከል የመጀመሪያ የነበረው የ1931 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት ስለዓለም አቀፍ ስምምነት በሚመለከት ያካተተው አንድ አንቀጽ ብቻ ነበር:: ይህም አንቀጽ 14 ነበር:: አንቀጹ ማናቸውንም ዓይነት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የመዋዋልና የመፈረም ሥልጣን የሰጠው ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ነበር:: እ.ኤ.አ. በ1941 ዓ.ም. ተደንግጎ ተፈጻሚነቱ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ከወጣ በኋላ ቀጥሎ በቆየው ትዕዛዝ ቁጥር 1 መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በስማቸው የመዋዋሉን ሥልጣን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው አስተላልፈዋል:: በዚህ ወቅት፥ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች አቋም ላይ ግንኙነት የነበረው ዋና ሕግ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ግዛት ጋር በፌዴሬሽን ስለማቀላቀል በሚመለከት ተደንግጎ የነበረው ትዕዛዝ ነበር::[7] በዚህ ትዕዛዝ አንቀጽ 8 መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ግዴታዎች ፌዴሬሽኑን ከሚመለከተው ድንጋጌና ከ1931 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት ጋር በመሆን በጊዜው በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል እውን በነበረው ፌዴሬሽን ክልል ውስጥ የሀገሪቱ ከፍተኛ ሕግ ደረጃ እንዲኖረው ተደርጎ ነበር::

ከ1931 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት ጋር ሲነጻጸር የተሻሻለው ሕገ መንግሥት የዓለም አቀፍ ስምምነትን የሚመለከቱ ብዛት ያላቸው አንቀጾችን ያቀፈ ነበር:: በአንቀጽ 30 እንደተመለከተው ሕገ መንግሥቱ ለሦስት የተለያዩ ዓይነት ስምምነቶች ዕውቅና ሰጥቶ ነበር:: እነዚህም፥ ማጽደቅ የማያስፈልጋቸው ስምምነቶች፥ ማጽደቅ የሚያስፈልጋቸው ስምምነቶችና ከመጽደቃቸው በፊት የፓርላማውን ፈቃድ የሚጠይቁ ስምምነቶች ነበሩ:: እንዲሁም ንጉሠ ነገሥቱ በተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ዲፓርትሜንቶች ከተፈረሙት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ውሎች መካከል የትኞቹ መጽደቅ ያስፈልጋቸው እንደሆነ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆኑን አንቀጹ የሚደነግግ ነበር::

---

[6] የኢትዮጵያ የሽግግር ጊዜ ቻርተር፥ 1991፥ አንቀጽ 1::

[7] የኤርትራን ግዛት ከኢትዮጵያ ንጉሠ መንግሥት ጋር በፌዴራል ስለማዋሀድና ስለመቀላቀል፥ ትዕዛዝ ቁጥር 6/1952፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 2ኛ ዓመት ቁጥር 1::

ከዚህም በተጨማሪ አንቀጽ 30 የፓርላማ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን የስምምነት ዓይነቶች ይዘረዝራል። እነዚህም፥ ሰላምን በሚመለከት የተደረጉ፥ በግል በኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ዕዳን የሚጭኑ፥ በሥራ ላይ የሚገኙ ሕጎች ላይ ለውጥን የሚያስከትሉ፥ ከመንግሥት ካዝና የገንዘብ ወጭን የሚያስከትሉ ወይም ብድር ወይም ሞኖፖሊዎችን የሚመለከቱ ስምምነቶች ነበሩ። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 88 እስከ 90 መሠረት ሁለቱም የፓርላማው ምክር ቤቶች ስምምነቶቹ በንጉሠ ነገሥቱ ከመጽደቃቸው በፊት ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን እንደነበራቸው ተደንግጓል። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 88 በተዘዋዋሪ እንደተገለጸውም፣ አንድ ስምምነት የሁለቱን የፓርላማ ምክር ቤቶች ፈቃድ ያገኘና ንጉሠ ነገሥቱም ፊርማቸውን ያስቀመጡበት እንደሆነ፣ የጽሕፈት ሚኒስቴር ስምምነቱ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎበት ነበር።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 122 መሠረትም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ግዴታዎች ከሕገ መንግሥቱ ጋር በመሆን የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆኑ ይቆጠሩ ነበር። ይሁን እንጂ በአንቀጹ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎች መካከል የነበረው አለመጣጣም በወቅቱ የኢትዮጵያን የሕግ ባለሞያዎች ለተለያዩ ክርክሮች ዳርጓቸው እንደነበር የሚታወስ ነው። እነዚህም በተለይ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ኢትዮጵያ ተቀብላቸው የነበሩትን ስምምነቶች ሁኔታና ስምምነቶችና ሕገ መንግሥቱ እርስ በርሳቸው ቅራኔ ሲፈጥሩ ስላለው ግንኙነት የሚመለከቱ ነበሩ።[8]

የ1980ው ዓ.ም. የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንዲሁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚመለከት ድንጋጌ ያካተተ ነበር።[9] በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 82(1)(መ) ውስጥ እንደተመለከተው፣ ብሔራዊ ሸንጎ በመባል ይታወቅ የነበረው ፓርላማ ቋሚ አካል በመሆን ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን እንዲኖረው ተደርጎ የነበረው የመንግሥት ምክር ቤት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እንዲያጸድቅና እንዲሽር ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር። በ1981 ዓ.ም. ተደንግጎ የነበረው ስለዓለም አቀፍ ስምምነቶች መዋዋል ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 25 በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እንዴት መዋዋል እንደሚቻል ማብራሪያን የሚሰጥ አዋጅ ነበር። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 3 እንደተመለከተውም የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስም ማንኛውንም ዓይነት ዓለም አቀፍ ስምምነት የመደራደርና የመዋዋል ሥልጣን የነበረውና ይህንንም እንዲያከናውኑ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ውክልና የመስጠት ሥልጣን እንደተሰጠው ይደነግጋል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ በአዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት ጥቂት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጉ የነበሩት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ ነበር። እነዚህም፣ አንደኛው፥ ሚኒስትሮችና ሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣኖች በመሥሪያ ቤታቸው ሥልጣን ሥር የሚገኙ የቴክኒክ ባሕሪ ያላቸው ጉዳዮችን

---

[8] አበራ ጀምበሬ፥ ስምምነቶች እንደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት የበላይ ሕግ፥ መመሪቂያ ወረቀት፥ የሕግ ፋኩልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ 1967፥ ገፅ 13-23 (ያልታተመ)።
[9] በወታደራዊው መንግሥት ወቅት ማለትም ከ1974 ሕገ መንግሥቱ ከሥራ ላይ እስከዋለበት እስከ 1987 ስምምነቶችን የማፅደቅ ሥልጣን የነበረው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ነበር። በ1967 የወታደራዊው አስተዳደር ደርግን ሥልጣን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ አንቀጽ 4 እና የወታደራዊው አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንን እንደገና ለመወሰን የወጣውን አዋጅ አንቀጽ 5 ይመልከቱ።

በተመለከተ ከተመሳሳይ የሌሎች ሀገሮች መሥሪያ ቤቶች ጋር የሚያደርጉት የጋራ ትብብር ስምምነቶች እና ሁለተኛው፥ ቀደም ሲል ያሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች በዋነኝነት የማስፈጸም ዓላማ የነበራቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚመለከቱት ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ በአንቀጽ 7 እንደተመለከተው፣ መሠረታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በሥራ ላይ ለመዋል የመጽደቅ አስፈላጊነትን የሚገልጹ ድንጋጌዎችን ያካተቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በመንግሥት ምክር ቤት እንዲጸድቁ ይደረግ ነበር።[10]

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሕገ መንግሥቶች ጋር በተያያዘ መልክ አንድ ሊጠቀስ የሚገባው ጠቃሚ ነጥብ አለ። ይህም የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1934ን የሚመለከት ነው። በዚህ አዋጅ መሠረት ፍርድ ቤቶች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ለሚወጡ ሕጎች ብቻ የሕግ ዕውቅና እንዲሰጡ ሀላፊነት ነበረባቸው። በመሆኑም በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ መውጣት ማንኛውም ሕግ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ሊሟላ የሚገባው እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ይቆጠር ነበር።[11] ሕግ የሚለው ቃል በትርጉሙ ሰፊ ቃል በመሆኑ በነጋሪት ጋዜጣ፥ የመታተም አስፈላጊነት በዓለም አቀፍ ስምምነቶችም ላይ እንዲሁ አግባብነት ነበረው። ይሁን እንጂ በእነዚህ ግዚያት የነበሩት ተሞክሮዎች እንደሚያስረዱት፣ በኢትዮጵያ ተቀባይነት ያገኙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ የማድረግ አስፈላጊነት ሁልጊዜ ተሟልቶ እንዲገኝ አልተደረገም።[12] በእነዚህ ጊዜያት ከጸደቁት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል አብዛኞዎቹ በነጋሪት ጋዜጣ አልታተሙም። በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ የተደረጉትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በተመለከተም ሙሉ ጽሑፎቻቸው በነጋሪት ጋዜጣ አልታተሙም። እንዲያውም የነበረው አሠራር፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የጸደቁ መሆናቸውን የሚገልጽ ድንጋጌ በአዋጅ ማውጣት ነበር። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ይህን አሠራር አልተከተለም። የቻርተሩ ሙሉ ጽሑፍ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ተደርጓልና ነው።[13]

## II. በፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት ወደ ዓለም አቀፍ ስምምነት የመግባት ሥነ ሥርዓት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፥ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ጨምሮ፥ ሁሉንም ዓይነት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የማጽደቅ ሥልጣን የሰጠው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55(12) ይህንኑ በግልጽ ያረጋግጣል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፌዴራል የሥልጣን ክልል ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም ጉዳዮች በተመለከተ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።[14]

---

[10] ሽፈራው ወልደሚኬል፥ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፀዳደቅ በኢትዮጵያ፥ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት፥ ቅጽ 13፥ ገፅ 157-167።

[11] የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1942፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 1ኛ ዓመት፥ አንቀጽ 5(ሀ)።

[12] ሽመልስ መታፈሪያ፥ የዓለም አቀፍ ስምምነት የማድረግ ሥልጣን በኢትዮጵያ፥ 1967፥ መመረቂያ ወረቀት፥ የሕግ ፋክልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ 1967፥ ገፅ 20 (ያልታተመ)።

[13] የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ማጽደቂያ አዋጅ፥ ቁጥር 202፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 22ኛ ዓመት ቁጥር 16።

[14] የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1)።

በሕገ መንግሥቱ መሠረት ለአስፈጻሚዊ አካል የተሰጠው ዓለም አቀፍ ስምምነትን የመደራደርና የመፈረም ሥልጣን ብቻ ነው፡፡ የፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 25(2) ውስጥ በግልጽ እንደተደነገገው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፥ አስፈጻሚውን በመወከልና አግባብነት ከአላቸው አካላት ጋር በመተባበር፥ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለመደራደርና ለመፈረም ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡[15] ከዚያም አስፈጻሚው የፈረመውን ስምምነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲደርሰው የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ስምምነቱ እንደደረሰውም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይት እንዲያደርግ ይጠበቅበታል፡፡ ተራ ሕግን ለማጽደቅ የሚከተለውን ተመሳሳይ መንገድ በመከተልም ምክር ቤቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቱን ሊያጸድቅ ይችላል፡፡ ምክር ቤቱ ስምምነቱን ያጸደቀው ከሆነ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ ይህንኑ ስምምነት፥ ምክር ቤቱ ስምምነቱን ማጽደቁን ከሚያረጋግጠው መግለጫ ጋር በአንድነት፥ በሁለት ቀናት ውስጥ ለፊርማ ወደ ሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የመላክ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 21(4)[16] እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 57 መሠረት ነው፡፡ የጸደቀው ዓለም አቀፍ ስምምነት በፕሬዚዳንቱ በተፈረመ ጊዜ ወይም ለፕሬዚዳንቱ ከደረሰ ከአሥራ አምስት ቀናት በኋላ የሕግ ኃይል ይኖረዋል፡፡[17] ይህም ዕውን የሚሆነው ስምምነቱ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ በማድረግ ነው፡፡[18]

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድን ዓለም አቀፍ ስምምነት ሲያጸድቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰነዱ ሁሉንም የማጽደቅ ፎርማሊቲዎች ማሟላቱን የማረጋገጥ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ በመሆኑም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ተገዥ መሆኗን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ወይም የማጽደቂያ ሰነድ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋዎች አዘጋጅቶ የማጽደቂያ ሰነዱ አስቀማጭ ለሆነው ሀገር ይልካል፡፡

በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት የማጽደቂያ ሰነድ በአስቀማጭ ሀገር እንዲቀመጥ ሲደረግ ዓለም አቀፋዊ ግዴታዎችን ያስከትላል፡፡[19] በመሆኑም፤ የማጽደቂያ ሰነዱ እንዲቀመጥ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ በግዛቷ ውስጥ የሕግ ኃይል ይኖረው ዘንድ ኢትዮጵያ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን የሕግ እርምጃዎች ሁሉ እንድትወስድ ትጠየቃለች፡፡[20] እነዚህም እርምጃዎች በተለይ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ መፈጠር ያለባቸውን ውስጣዊ ሁኔታዎች ማመቻቸትን ያካትታሉ፡፡[21] ይህ ሂደት በሚከተሉት ክፍሎች ማለትም የዓለም አቀፋዊ ሰብዓዊ መብቶች የውስጥ አፈጻጸምና ደረጃ በሚሉ ሁለት ታላላቅ ርዕሶች አማካይነት ይመረመራል፡፡

---

[15] የኢፌድሪ የሕግ አስፈፃሚ አካልን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ፥ ቁጥር 2፥ አንቀጽ 25(2)፡፡
[16] የተወካዮች-ምክር ቤት ሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት፥ ቁጥር 4/1995፥ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፥ 1ኛ ዓመት፥ ቁጥር 2፥ አንቀጽ 25(2)፡፡
[17] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀጽ 8(2)፡፡
[18] የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 71(2)፡፡
[19] የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር፥ አንቀፅ 102፡፡
[20] የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግ፤ ሀገሮች በአጸደቋቸው ስምምነቶች ውስጥ የተረጋገጡ መብቶችና ነፃነቶች ተፈጻሚ ይሆኑ ዘንድ አስፈላጊውን እርምጃ ማለትም የሕግ ማውጣት፥ አስተዳደራዊ፥ የዳኝነት ኢኮኖሚያዊ፥ ማሕበራዊ፥ እንዲሁም ትምህርታዊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠይቃል፡፡
[21] ካርል ጆሴፍ ፓርሽ፥ ዓለም አቀፍ ሕግ እንደ ብሔራዊ ሕግ አካል፥ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግ ብሔራዊ አፈፃፀም፥ 1990፥ ገጽ 1-2፡፡

## III. የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የውስጥ አፈጻጸም

የጸደቁ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖራቸው አፈጻጸም ላይ የሚደረግ ውይይት ሁለት የተለያዩ የሕግ ሁኔታዎችን መመርመር ይጠይቃል:: በአንድ በኩል የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(4) "በኢትዮጵያ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሁሉ የሀገሪቱ ሕግ አካል" መሆናቸውን በግለጽ ያመለክታል::

በሌላ በኩል ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲጸድቁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ እንዲያደርግ ለፌዴራሉ ፕሬዚዳንት ሥልጣን ይሰጠዋል:: ሕገ መንግሥቱ እንደሚከተለው ይደነግጋል፤

> በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቃቸውን ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ ያወጣል::"

ከዚህ ጋር በማያያዝ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1987ትን በተጨማሪ መጥቀስ አስፈላጊ ነው:: ይህ አዋጅ የቀድሞውን ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1943ን የተካ አዋጅ ነው:: የፌዴራሉ ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 2(3) እንዲህ ይነበባል፤

> "ሁሉም የፌዴራል ወይም የክልል ሕግ አውጪ፥ አስፈጻሚና ዳኝነት አካላት እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰው በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ለሚወጡ ሕጎች እውቅና ይሰጣል::"[22]

እዚህ ላይ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ይሆናል:: በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(4) ትርጉም መሠረት ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደጸደቁ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ? በሌላ አነጋገር የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የኢትዮጵያ ሕግ አካል እንዲሆኑ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው መውጣታቸው እንደ ቅደም ሁኔታ መታየት አለበት? በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ ይደረጋል ማለት እንደነዚህ ያሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የመውጣት አስፈላጊነትን ሳያሟሉ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ውጤት አይኖራቸውም ማለት ነው?

በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት ንዑስ ክፍሎች ይገኛሉ:: የመጀመሪያው ከዚህ በላይ የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመርመር ይሞክራል:: ሁለተኛው ደግሞ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን የኢትዮጵያ ሕግ አካል ለማድረግ በሥራ ላይ ሊውሉ በሚችሉ የማተም ዘዴዎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል::

---

[22] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 71(2)::

## ሀ. የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ስለማተም

በአንድ ሀገር ውስጥ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ስለማተም ከሚደረገው ውይይት ጋር በተያያዘ መልኩ ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና ያገኙ ሁለት መሠረተ ሀሳቦች አሉ:: በአንድ በኩል፤ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የማጽደቅ ተግባር[23] ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን ባለው አካል ሲፈጸም ስምምነቶቹ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ መድረኮች ላይ የሕግ ኃይል ያገኙ መሆኑን ጭምር እንደሚያረጋግጥ ይቆጠራል::[24] በሌላ በኩል፤ አንድ ሀገር ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በግዛቷ ውስጥ ውጤት ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ለመወሰን ሥልጣን ያላት መሆኑን ዓለም አቀፍ ሕግ ዕውቅና ይሰጣል:: በሌላ አነጋገር፤ አንድ ሀገር ያጸደቃቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በግዛቷ ውስጥ ተፈጻሚ የምታደርገው የሕገ መንግሥቷ ድንጋጌዎች በሚፈቅዱት መሠረት ነው:: ለምሳሌም፤ የዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ ስምምነት አንድ አባል ሀገር በስምምነቱ የተረጋገጡትን መብቶችና ነፃነቶች በሀገሩ "ሕገ መንግሥታዊ ሂደት" እና በራሱ በስምምነቱ መሠረት" በሥራ ላይ እንዲውሉ ይጠይቃል:: ይህም ሁኔታ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በየግዛታቸው ውስጥ የሕግ ውጤት እንዲኖራቸው እንደቅድመ ሁኔታ ከሚታየው የማተም ሁኔታ ጋር በተያያዘ መልክ ሀገሮች የተለያዩ መንገዶችን እንዲከተሉ አስችሏቸዋል::

በዚህ ጉዳይ ላይ ሀገሮች በሁለት ቡድኖች ሊከፈሉ ይችላሉ:: የመጀመሪያው ቡድን የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በየብሔራዊ የሕግ ነጋሪት ጋዜጣዎቻቸው ውስጥ ታትመው እንዲወጡ ሕገ መንግሥቶቻቸው የሚያስገድዷቸውን ሀገሮች ያካትታል:: ለምሳሌ፥ በፈረንሳይ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ታትመው እንዲወጡ ማድረግ መሟላት ያለበት የሕግ ሁኔታ ነው::[25] በጀርመን ተቀባይነት ባገኘው አመለካከት መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወደ ብሔራዊ ሕግ ሥርዓት አካልነት እንዲለወጡ የሚደረጉት የመንግሥት ባለሥልጣናትና ሕዝቡ ያውቃቸው ዘንድ በሕግ አውጪው በሕግ መልክ እንዲወጡ ሲደረግ ነው::[26] በስዊዘርላንድ፤ በአንድ በኩል የመንግሥት አካላት ያልታተሙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ የሚገደዱ ቢሆንም በሌላ በኩል እንደነዚህ ያሉ ስምምነቶች በግለሰቦች ዘንድ አስገዳጅነት የሚኖራቸው በሕግ ጋዜጣ ታትመው ሲገኙ ብቻ ነው::[27] በፖርቱጋልና[28] በቱርክ[29] ሕጎች፤ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የማተም ተግባር እነዚህኑ ስምምነቶች የብሔራዊ ሕግ አካል የማድረግ ዘዴ እንደሆነ በግልጽ ተገልጿል:: በቤልጂግ ሕግ፤ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ

---

[23] ማጽደቅ ማለት፥ አንድ ሀገር ላደረገው ስምምነት በዓለም አቀፍ መድረክ እራሱን ተገዥ ማድረጉን መግለፅ ማለት ነው::

[24] የቁጥር 1 ውሳኔ ፕሮጀክት አንቀጽ 2 ስለመሠረታዊ ዓለም አቀፍ ሕግ እንደሚከተለው ያስነብባል፤ "ፖዚቲቭ የዓለም አቀፍ ሕግ የእያንዳንዱን ሀገር ሕግ ከፊል ክፍል ይይዛል:: ይህም የሚሆነው የእያንዳንዱ ሀገር ሕገ መንግሥት ከሚያስቀምጣቸው ፖለቲካዊ መለኪያዎች ጋር በተገናዘበ መልክ ነው::" የውሳኔው ሙሉ ቃል በአሜሪካ የዓለም አቀፍ ሕግ መጽሔት ቅፅ 2፥ 1928፥ ገጽ 238-239 ውስጥ ተካቷል::

[25] የ1958 እ.ኤ.አ. የፈረንሳይ ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 55::

[26] እንድሪው ዚድ ድርዜንቼውስኪ፥ የአውሮፓ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በሀገር ውስጥ ሕግ፥ ንጽጽራዊ ጥናት፥ 1985፥ ገፅ 108::

[27] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 119::

[28] የሚያዝያ 25 ቀን 1976 የፖርቱጋል ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 8(2)::

[29] የ1961 የቱርክ ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 65(1)::

መብት ስምምነቶች በግለሰቦች ላይ አስገዳጅነት የሚኖራቸው እነዚሁ ግለሰቦች በህትመት አማካይነት እንዲያውቋቸው የተደረጉ እንደሆነ ብቻ ነው::[30]

በእንግሊዝ ሕግ፣ አጠቃላይነት ባለው ልምድ እንደሚታየው፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ሊሆኑ የሚችሉት በእንግሊዝ ፓርላማ ውሳኔ መሠረት ሕግ እንዲሆኑና እንዲታተሙ እስከተደረገ ነው::[31] በአርጀንቲና፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የፌዴራሉ ሕግ አካል የሚሆኑት በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 31 መሠረት የታተሙ እንደሆነ ነው::[32] ክሮሺያን[33] ጨምሮ በብዙ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ታትመው እንዲወጡ ማድረግ የብሔራዊ ሕግ አካል ሆነው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል::[34]

የሁለተኛው ቡድን ሀገሮች፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተፈጻሚነት ያገኙ ዘንድ ህትመትን እንደ ቅደመ ሁኔታ አድርገው አይቆጥሩም:: ዩናይትድ ስቴትስ እንደ አንድ ምሳሌ ሆና ልትጠቀስ ትችላለች:: በዩናይትድ ስቴትስ ከሴኔት አባላት መካከል የሁለት ሦስተኛውን አብላጭ ድምጽ ድጋፍ አግኝቶ በፕሬዚዳንቱ የጸደቀ ዓለም አቀፍ ስምምነት በኦፊሴላዊ አዋጅ ታትሞ እንዲወጣ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም::[35] በመሆኑም የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ባይታተሙም እንኳ ውጤት እንዲኖራቸው የማድረግ ግዴታ አለባቸው:: ይሁን እንጂ፣ እንደነዚህ ያሉ ስምምነቶች በዓለም አቀፍ መድረክ ተፈጻሚነትን ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል::

አንድ ሀገር፣ ዓለም አቀፍ ሕግና ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅድለት መሠረት፥ አንድን ዓለም አቀፍ ስምምነት ሲያጸድቅ ስምምነቱን በሙሉ በግዛቱ ውስጥ ዕውን ሊሆን የሚረዱትን ማናቸውንም እርምጃዎች ለመውሰድ ግዴታ መግባቱ ነው::[36] ከእነዚህም እርምጃዎች መካከል አንዱ ዓለም አቀፍ ስምምነቱን የሀገሩ ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ነው:: ይህም ዕውን ሊሆን የሚችለው የጸደቀው ስምምነት ታትሞ እንዲወጣ በማድረግ ብቻ ነው::

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ ውጤት ያገኙ ዘንድ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልግ ወይም አያስፈልግ እንደሆነ ግልጽ አይደለም:: በዚህ ጉዳይ ላይ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አመለካከቶች ይንፀባረቃሉ:: እነዚህ አመለካከቶች በተለይ እ.ኤ.አ. ከግንቦት 18 እስከ 22/1998 ዓ.ም

[30] ዴቪድ አር ዲነር፥ በብሔራዊ ሕግና የዓለም አቀፍ ስምምነት መካከል ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በፊት የነበሩ አንዳንድ የግንኙነት አቅጣጫዎች፥ የህንድ ዓለም አቀፍ ሕግ መፅሔት፥ ቅፅ 5፥ ቁጥር 3፥ ሐምሌ 1965፥ ገፅ 271፣ እንዲሁም አንድሪው ዜድ ድርዜንቼውስኪ ገፅ 643 ይመልከቱ::

[31] አር እና ዋና የስደተኞች ቢሮ፥ ኤክስፔንቴ ሳላማት ቢቢ (1976)1 ደብሊው ኤል አር 979::

[32] አንቀጽ 19፥ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ማንዋል፥ ዓለም አቀፍና ኮምፓራቲቭ ሕግ ደረጃዎችና ሥነ ሥርዓት፥ 1993፥ ገጽ 44::

[33] የታህሳስ 33 1999 የክሮሺያ ሕገ መንግሥት፥ አንቀጽ 134::

[34] ኤሪክ ስቴን፥ ዓለም አቀፍ ሕግ በሀገር ውስጥ ሕግ፥ የመካከለኛው ምሥራቅ አውሮፓ ሕገ መንግሥት ዓለም አቀፋዊነት አቅጣጫ፥ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ሕግ መፅሔት፥ ቅፅ 88፥ ቁጥር 3፥ 1994፥ ገፅ 444::

[35] ኢሬድስና ጉልድ፥ የዓለም አቀፍ ሕግና የብሔራዊ ሕግ ግንኙነት በአሜሪካ እና በኔዘርላንድስ፥ 1961፥ገፅ 305-307::

[36] በዓለም አቀፍ ሕግ ውስጥ አንድ ሀገር ስምምነትን ሲያፀድቅ ወይም ለስምምነት ሲገዛ ያ ሀገር ራሱን ለዛ ስምምነት አስገዝቶ መብትንና ነፃነትን ለማክበር መዘጋጀቱን ያመለክታል:: ለምሳሌ፥ አንቀጽ 2 (1) የተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነትን ይመልከቱ::

የኢትዮጵያን ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የእንባ ጠባቂ መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም ተካሂዶ በነበረው ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስና እ.ኤ.አ. ከግንቦት 19 እስከ 20/2000 ዓ.ም. "ሕገ መንግሥቱን ከማስከበር ረገድ የፍርድ ቤቶች ሚና" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ አዘጋጅነት በተካሄደው ሲምፖዚየም ተንደባርቀው ነበር፡፡ ኮንፈረንሱና ሲምፖዚየሙ የተካሄዱት በአዲስ አበባ፥ በኢትዮጵያ ነበር፡፡

የመጀመሪያው አመለካከት፣ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተወካዮች ምክር ቤት መጽደቅ እነዚሁ ስምምነቶች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ውጤት እንዲኖራቸው ያስችላል የሚል ነው፡፡ አቋማቸውንም ለማጠናከር እንዲረዳቸው በማሰብ የዚህ አመለካከት አራማጆች የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥትን አንቀጽ 9(4) ይጠቅሳሉ፡፡ በእነዚህ ሕግ ባለሞያዎች እንደሚቀርበው ክርክር፣ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት የኢትዮጵያ ሕግ አካል የሚሆነው ስምምነቱ እንደጸደቀ ወዲያውኑ ነው፡፡ እነዚህ ሕግ ባለሞያዎች የስምምነቱ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ መውጣት በመጽደቅ ተግባር ቀድሞውኑ ሕጋዊ እንዲሆን ለተደረገው ስምምነት ሕጋዊነትን የሚጨምር አይሆንም በማለት ያስረዳሉ፡፡[37] በመሆኑም፣ በዚህ አመለካከት መሠረት የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ ሳያስፈልግ ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሌላው አመለካከት ተቃራኒ አቋምን የያዘ ነው፡፡ ይህ አመለካከት፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው በነጋሪት ጋዜጣ የመታተማቸውን አስፈላጊነት በመደገፍ ይከራከራል፡፡[38] በዚህ አመለካከት መሠረት፣ በነጋሪት ጋዜጣ የማተም አስፈላጊነት፥ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደተደነገጉ ሕጎች ሁሉ፥ በጸደቁ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችም ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡ የዚህ አመለካከት አራማጆች አዘውትረው የሚጠቅሱት የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1987 አንቀጽ 2(3)ትን ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ደራሲ፥ በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች በመመርኮዝ፥ ከሁለተኛው አመለካከት ጋር ይስማማል፡፡

የመጀመሪያው ምክንያት፣ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ጋር በተጣጣመ መልክ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቁትን ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ እንዲያውጅ የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንት ከሚጠይቀው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71(2) የሚገናኝ ነው፡፡ ይህንን ድንጋጌ በቅርብ ከመመርመር መረዳት እንደሚቻለው አንቀጹ የተደነገገው ግልጽ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ነው፡፡ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች እንደሌሎች ሕጎች ሁሉ የተወካዮች ምክር ቤት የውይይት ውጤቶች መሆናቸው የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ሕዝቡ እንዲያውቃቸው ሊደረጉ የሚችሉት በነጋሪት

---

[37]ግርማ አማረ፥ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ሥርዓት፥ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥትና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች፥ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የእንባ ጠባቂ ተቋምን ስለማቋቋም ስብሰባ በተካሄደበት ወቅት የቀረበ ወረቀት፥ ከግንቦት 18-22፥ 1998 አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ፡፡

[38] ኢብራሂም ኢድሪስ፥ የወደፊት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምን መሆን አለበት፥ 1998፥ ገፅ 22፥23 የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና የእምባ ጠባቂ ተቋምን ስለማቋቋም በተካሄደ ስብሰባ ወቅት የቀረበ፥ ከግንቦት 18-22፥ 1998፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ፡፡

ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ ሲደረግ ነው፡፡[39]

ይህ የክርክር ነጥብ የ1987ትን የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ወደሚመለከተው ሁለተኛው ምክንያት ይመራናል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(3) መሠረት የፌዴራል ሕጎች በፍርድ ቤት እንዲታወቁና ተፈጻሚነትንም ያገኙ ዘንድ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙ ማድረግ ፍጹም አስፈላጊ ነው፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 14/1988 አንቀጽ 2(1) ሕጎች በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚነትን ያገኙ ዘንድ የመታተማቸውን አስፈላጊነት እንዲሁ ያስምርበታል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) እንደሚከተለው ይነበባል፤

> 'ሕግ' ማለት በዚህ አዋጅ በተደነገገው ሥነ ሥርዓት መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ በፕሬዚዳንቱ ፊርማ አማካኝነት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ የሚውል ሕግ፥ ደንብ ወይም መመሪያ ነው፡፡"

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፤ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቁና በአዋጅ መልክም በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙ ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ስምምነቶች እንደማናቸውም ሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች የሚታዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ሕግ፤ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀ አንድ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በሀገሪቱ ውስጥ ተፈጻሚ የሚሆነው በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ በአዋጅ አማካይነት የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት አካል እንዲሆን የተደረገ እንደሆነ ነው፡፡ በእርግጥም፤ ሕትመት አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በኢትዮጵያ ውስጥ ውጤት እንዲያገኝ የሚያስችል ተግባር ነው፡፡

## ለ. <u>ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን የማተም ዘዴዎች</u>

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ከፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ትርጉም አንጻር ምርመራ ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ከማተም ዘዴ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከትም፤ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ህትመት ዕውን የሚሆንበት ቢያንስ ሦስት የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚህም፤ ሀ/ የጸደቀን ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ሙሉ ቃል ከአዋጁ ውስጥ መደንገግ፤ ለ/ ስምምነቱ መጽደቁን ብቻ የሚያመለክት ሕግ ማውጣት፤ እና ሐ/ ስምምነቱ ወይም አግባብነት ያላቸው የስምምነቱ ድንጋጌዎች

---

[39] የጸደቁ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በተወሰነው በ15 ቀናት ውስጥ ባለመጽደቃቸው ተፈጻሚነት የሚያገኙበት ዕውነታ ልዩ ባህሪ ያለው ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ነገር ቢያጋጥምም፤ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በአንድ ዓይነት የሕትመት ዘዴ፥ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አማካይነት፥ በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቁ ከመደረጉ በፊት በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የሚቻል አይመስልም፡፡ በእርግጥ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ማውጣት ሥነ ሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 8(2) በግልጽ እንደተደነገገው በምክር ቤቱ የተደነገጉ ሕጎች፥ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ጨምሮ፥ በሪፐብሊክ ፕሬዚዳንቱ ያልተፈረሙ ከሆነ ምክር ቤቱ ሕጎቹን የማተም ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በሕግ ውስጥ ተካተው እንዲወጡ ማድረግ፣ የሚሉት ናቸው::[40]

ከእነዚህ ሦስት የህትመት ዘዴዎች መካከል ኢትዮጵያ የትኛውን የመረጠች ስለመሆኑ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ግልጽ አይደለም:: የሀገሪቱ የሕግ ማውጣት ልምድ እንደሚያረጋግጠው ከሆነ፣ ከሦስቱ ዘዴዎች መካከል አንዱ ወይም ሌላው በቋሚነት ተከታይነትን አላገኘም:: በእርግጥ፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በአንዱ ወይም በሌላው ዘዴ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ የተደነገጉባቸው ምሳሌዎች አሉ:: የመጀመሪያውን ዘዴ በተመለከተ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል:: የአፍሪካ አንድነት ቻርተር፥ ምንም እንኳ የሰብዓዊ መብት ሰነድ ባይሆንም፥ ይህ ጸሐፊ እስከሚያውቀው ድረስ፣ የእንግሊዝኛው ሙሉ ቃል ከአማርኛ ትርጓሜው ጋር በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ የተደረገ ብቸኛ ስምምነት ነው:: [41] የሕፃናት ዓለም አቀፍ ስምምነትንና[42] የኬሚካል መሣሪያዎች ስምምነትን[43] በሥራ ላይ ለማዋል የወጡት አዋጆች የሁለተኛው ዘዴ ምሳሌዎች ናቸው:: ይህን ዘዴ በሥራ ላይ ማዋልን በተመለከተ፣ የማጽደቂያ አዋጆቹ የጸደቁ ስምምነቶቹን በመጥቀስ ብቻና የስምምነቶቹን ሙሉ ቃል ሳይዙ ወይም አባሪ ሳያደርጉ እንዲደነገጉ ይደረጋል::[44] ከውጭ መንግሥታት ወይም ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ የብድር ውሎች በነጋሪት ጋዜጣ የሚታተሙ የማጽደቂያ ድንጋጌ ዘዴ ምሳሌዎች ናቸው:: እንደዚህ ያሉት አዋጆች የሚያሳዩት ዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ መጽደቃቸውን ብቻ ነው:: ሦስተኛውን ዘዴ በተመለከተ ደግሞ፣ በሰው ዘር ላይ የሚፈጸም ጥፋትን የሚመለከተው ስምምነትና እ.ኤ.አ. በ1949 ዓ.ም. የተደረጉት አራቱ የጄኔቫ ስምምነቶች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው:: ስምምነቶቹ እንዲጸድቁ ከመደረጋቸው በተጨማሪ ዋና ዋና ድንጋጌዎቻቸው አግባብነት ባለው የኢትዮጵያ ሕግ፥ ማለትም በ1949 የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፥ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል::[45]

በዚህ ጸሐፊ አመለካከት፣ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሙሉ ቃል ታትመው እንዲወጡ የማድረግ አስፈላጊነትን መቀበል በኢትዮጵያ በኩል ዓለም አቀፍ ሕግን በእርግጥ እንደማክበር የሚቆጠር ነው::[46] ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ልዩ ባህሪ ያላቸው ስምምነቶች ናቸው:: አስተዳደርን ብቻ ከሚመለከቱ ሌሎች የስምምነት ዓይነቶች ጋር ሲነጻጸሩ፣ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ተፈጻሚ ይሆኑ ዘንድ በሕዝቡ ዘንድ ዕውቅና እንዲያገኙ መደረግ የሚገባቸው የተለዩ የስምምነት ዓይነቶችን የሚወክሉ ናቸው:: ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የሰዎችን መብቶች፥ ነፃነቶችና ግዴታዎች የሚመለከቱ ናቸው:: ግለሰቦችና ቡድኖች የጸደቁ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን፥ ድንጋጌዎችንና መርሆዎችን በመጥቀስ እራሳቸውን መከላከል የሚችሉት

---

[40] አን ኤፍ ቤፍስኪ፥ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግ፥ በካናዳ የመብት ቻርተርና በመክሰስ መብት ውስጥ አጠቃቀም፥ ጥቅምት 1992፥ ገፅ 32-33::

[41] የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ማጽደቂያ አዋጅ፥ ቁጥር 2021/1963፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 22ኛ ዓመት፥ ቁጥር 16::

[42] የሕፃናት ሐብት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ፥ ቁጥር 10/1992፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 51ኛ ዓመት፥ ቁጥር 5::

[43] የኬሚካል መሣሪያዎችን መሥራት፥ ማምረት፥ ማከማቸት፥ መጠቀም የሚከለክለውና ስለመውደማቸው የሚመለከተውን ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ፥ ቁጥር 30/1996፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 51ኛ ዓመት፥ ቁጥር 18::

[44] ይህ ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጪ አበዳሪ አገሮች ጋር ያደረገችውን የብድር ስምምነት ያጠቃልላል::

[45] የ1949 የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፥ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ፥ አንቀጽ 281 እና 282ን በዘር ማጥፋትና ሰብዓዊነት ላይ ስለሚደረግ ወንጀል በቅደም ተከተል አጠቃሎ ይዟል::

[46] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፥ አንቀፅ 71(2)::

ስለነዚሁ ስምምነቶች መኖር የሚያውቁ እንደሆነ ነው::[47] ስምምነቶች በፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ካላቸው ተፈጻሚነት ጋር በተያያዘ መልኩ ላውረንስ ፔርስስ እንዲህ በማለት ጽፏል፤

> ሕትመት ዜጎች ስለዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲያውቁ ያደርጋል፥ ግዴታዎቻቸው የሚመነጩበትን ሁኔታ ለመረዳትና መብቶቻቸውንም በፍርድ ቤቶችና በሌሎች የመንግሥት አካላት ፊት እንዲያስከብሩ ይረዳል::"

በመሆኑም እንደሌሎቹ የሀገሪቱ ሕጎች፤ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ሕዝብ በሚረዳው ቋንቋ እንዲያውቃቸው ጉዳዮችን በሚያስተናግዱ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ እንዲታተም ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በኢትዮጵያ ከፌዴሬሽኑ አባላት መካከል በቤንሻንጉል፥ በጋምቤላና በደቡብ ብሔሮች፥ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን የሚያስችሉት በፌዴራል መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ በሆነው በአማርኛ ነው::[48] ይህም ሁኔታ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሙሉ ቃል በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣዎች ታትመው የመውጣታቸውን አስፈላጊነት ያሳያል::[49] "ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም" የሚለው የሕግ አባባል የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ሙሉ ቃል ሕዝቡ እንዲያውቃቸው የማድረግ ጠቃሚነትን ያጠናክራል። በእርግጥ ከዚህ አመለካከት በመነሳት ነው የሕፃናት መብትን የሚመለከተው ኮሚቴ በ371ኛ ስብሰባው ኢትዮጵያ የሕፃናት ኮንቬንሽንን ሙሉ ቃል ማተም ያለባት መሆኑን ያሳሰበው::[50]

የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ፤ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በሕግ ጋዜጦች ታትመው እንዲወጡ የማድረግ አስፈላጊነትን አሳስቧል:: ይህንንም ማሳሰቢያ የሰጠው ከተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ ዓለም አቀፍም ሰነድ ጋር በተያያዘ ነበር። በ311ኛ ስብሰባው፤ ኮሚቴው ይኸው ሰነድ የስምምነቱ ተዋዋይ በሆነ አባል ሀገር ሁሉ በሁሉም ቋንቋ ተተርጉሞ በሕግ ጋዜጣዎች እንዲወጣ አቋም ወስዷል::[51] እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ግለሰቦች በሰነዱ ውስጥ የተካተቱ መብቶቻቸውን ለማወቅና እንዲሁም የአስተዳደር ባለሥልጣናትና ዳኞች ተዋዋይ ሀገሩ በስምምነቱ መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች እንዲገነዘቡ የሚያስችላቸው ስለመሆኑ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴው እምነቱን ገልጿል::

በእርግጥ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጡ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በሥራ መዋላቸው እየተጠናከረ ሊመጣ የሚችለው ሕዝቡ ስለእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች እንዲያውቁ የተደረገ ከሆነ ነው:: ስምምነቶቹ ባልታተሙበት ሁኔታም ሕዝቡ መብቶቹንና ነፃነቶቹን ስለማወቁ አጠራጣሪ ነው:: ይህም መሠረታዊ

---

[47] ላውረንስ ፐሪየስ፥ በፈረንሳይ ሕገ መንግሥት ሥርዓት የዓለም አቀፍና የብሔራዊ ሕግ ግንኙነት፥ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ሕግ መፅሔት፥ ቅፅ 44፥ 1950፥ ገጽ 650-651::

[48] የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት፥ አንቀፅ 50(2) እንዲህ ይነበባል:- "አማርኛ የፌዴራል መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ ነው"::

[49] የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ፥ አንቀፅ 5፥ እንዲህ ይነበባል:- "የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይታተማል። በሁለቱ መካከል አለመጣጣም በሚኖርበት ወቅት አማርኛው የበላይነት ይኖረዋል"::

[50] የሕፃናት መብት ኮሚቴ ለ37ኛ ጊዜ ሲገናኝ ያጠቃለለው አመለካከት (24ኛ ስብሰባ) ጥር 24 1997 የተካሄደ፤ ገጽ 7::

[51] አጠቃላይ አስተያየት፥ ቁጥር 3(13)፥ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ፥ ሐምሌ 28፥ 1981::

መብቶችና ነፃነቶች ሊጣሱ የሚችሉበት ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማድረጉ አያጠራጥርም:: ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የፌዴራሉ መንግሥት ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በቀላሉ ለሕዝቡ እንዲደርሱ የማድረግ አስፈላጊነትን የተረዳው ይመስላል:: እንዲያውም ይህን ተግባር የማከናወን ኃላፊነት በአሁኑ ጊዜ ሥራውን ገና መሥራት ላልጀመረው ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ተሰጥቷል:: በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት ከኮሚሽኑ ተግባሮች መካከል አንዱ "በኢትዮጵያ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሰነዶችን ወደ ብሔራዊ ቋንቋዎች መተርጎምና ማሠራጨት" እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል::[52] እንደነዚህ ያሉ ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ተፈጻሚ እንዲሆኑ በይፋ በታወቁ ቋንቋዎች በፌዴራልና በክልል ነጋሪት ጋዜጣዎች ሊታተሙ ይገባል::

ለመግለጽ አስፈላጊ ባይሆንም፣ እንደ ብድር፥ ህብረት መፍጠርን፥ ዓለም አቀፍ አለመግባባቶችን በስምምነት መጨረስ፥ የመሣሪያ ቅነሳንና በጋራ መረዳዳትን በመሰሉ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ስምምነቶች በአስተዳደሩ ላይ ብቻ ውጤት ያላቸው ናቸው:: በመሆኑም እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ሌሎች ስምምነቶችን በተመለከተ የስምምነቶቹን ሙሉ ቃል ማተም ሳያስፈልግ የማጽደቂያ ድንጋጌዎችን ብቻ ማውጣት በቂ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም በእንደነዚህ ያሉ ጉዳዮች የስምምነቶቹ ሙሉ ቃል በነጋሪት ጋዜጣዎች ታትመው አለመውጣታቸው አስተዳደሩ ስለስምምነቶቹ ይዘት ዕውቀት የለውም ከሚል ድምዳሜ አያደርስም:: በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለጸደቁ ስምምነቶች ተዋዋይ የሆነው የመንግሥት አስተዳደር አካል ስለስምምነቶች ዕውቀት ያለው መሆኑ ይገመታል::

## IV. የጸደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ደረጃ በኢፌድሪ ሕገ መንግሥት

በዓለም አቀፍ ሕግ ፍልስፍና ውስጥ፣ ዓለም አቀፍ ሕግ ከብሔራዊ ሕግ ጋር ያለው ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ፣ ማለትም ከዓለም አቀፋዊና ከብሔራዊ አቅጣጫዎች አንጻር ሊታይ ይችላል::[53] ከዓለም አቀፋዊ አቅጣጫ አንጻር፣ ማለትም ብሔራዊ ሕግ በዓለም አቀፉ መድረክ ውስጥ ያለውን ሥፍራ በተመለከተ፣ ተቀባይነት ያገኘው አመለካከት ዓለም አቀፋዊ ሕግ በሀገሮች ላይ አስገዳጅነት አለው፣ ሀገሮች ዓለም አቀፍ ሕግን በየግዛታቸው ውስጥ እንዲከበር የማያደርጉ ከሆነ የሕግ ኃላፊነትን ያስከትልባቸዋል የሚለው ነው:: በዚህም አመለካከት መሠረት፣ ሀገሮች በምንም መንገድ ቢሆን ከዓለም አቀፍ ግዴታዎቻቸው እራሳቸውን ለማውጣት ሲሉ በሕገ መንግሥቶቻቸው ወይም በሕጎቻቸው ሊመኩ አይችሉም:: ይህን የዓለም አቀፍ ሕግ በብሔራዊ ሕግ ላይ ያለውን የበላይነት ቦታ አጽንኦት በመስጠት እ.ኤ.አ. በ1969 ዓ.ም. የተደረገው የቬና ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 27፣ የአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ተዋዋይ የሆነ ስምምነቱን ተፈጻሚ ላለማድረግ በማሰብ ብሔራዊ ሕጉን መጥቀስ አይችልም ብሎ በማለት አጠብቆ ይደነግጋል::

ይህንንም አቋም የዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራንና የዓለም አቀፍ ፍርድ ሸንጎዎች የሚደግፉት ነው:: የዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን የዓለም አቀፍ ሕግን የበላይነት በመደጋገም ያሳስባሉ፣ ሀገሮች ዓለም አቀፍ ግዴታዎቻቸውን ለመጣስ የብሔራዊ

---

[52] የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋም አዋጅ፥ ቁጥር 210/20000፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 6ኛ ዓመት፥ ቁጥር 40 አንቀጽ 6(8)::
[53] ማልኮም ኤን ሻው፥ የዓለም አቀፍ ሕግ፥ 2ኛ እትም፥ 1986፥ ገጽ 100-103::

ሕጎቻቸውን እንደ ምክንያት የሚጠቅሱበትንም አካሄድ ይቃወማሉ::[54] ዓለም አቀፍ የፍርድ ሸንጎዎችን በተመለከተ ደግሞ ከቋሚው የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተሰንዝረው የነበሩ ሀሳቦች በእርግጥ በጣም ከፍተኛ አስተዎጽኦ ነበራቸው:: በብዙ በቀረቡለት ጉዳዮች ላይ በሰጣቸው ውሳኔዎች ቋሚው የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከዓለም አቀፍ ሕግ ጋር የሚቃረን ብሔራዊ ሕግ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ወስኗል::[55] ለምሳሌ የፓላንድ ዜጎች በዳንዚንግ እ.ኤ.አ. በ1931 ዓ.ም. በተወሰነው ጉዳይ፤ ፍርድ ቤቱ አንዲ ሀገር በሥራ ላይ ባለ ዓለም አቀፍ ስምምነት የተጣሉበትን ግዴታዎች ለመሸሽ በማሰብ በራሱ ሕገ መንግሥት መተማመን እንደማይችል ሀሳቡን ገልጿል::[56]

ይሁን እንጂ፤ ከሀገር ውስጥ አቅጣጫ አኳያ ሲታይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በብሔራዊ ሕጎች ውስጥ ያላቸውን ደረጃ መወሰን በሀገሮች ዘንድ የተለመደ አሠራር ነው:: እንዲህ ያለውም የሀገሮች አሠራር በፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና በብሔራዊ ሕጎች መካከል ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል:: በመሆኑም አንድ የፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ከሀገሩ ሕገ መንግሥት፥ በእኩል ደረጃ ከሚገኙ ቀደም ሲል ወይም ኋላ ከወጡ ብሔራዊ ሕጎች፥ እና ከሌሎች ሕጎች ጋር ግጭት ሊፈጥር ይችላል::

## ሀ. የፀደቁ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት

የፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ከአንድ ሀገር ሕገ መንግሥት ጋር ሊጋጭ ይችላል:: በዚህም ጊዜ፥ በሚመለከተው ሀገር ሕገ መንግሥት ወይም ሕግ መሠረት ዓለም አቀፉ ስምምነት ከሕገ መንግሥቱ የበላይ የሆነ ደረጃ ሊሰጠው፥ ከሕገ መንግሥቱ ጋር በእኩል ደረጃ ሊታይ፥ ወይም ከሕገ መንግሥቱ የበታች የሆነ ደረጃ ሊያገኝ ይችላል:: በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ሀገሮች ተመሳሳይ አሠራርን ላይከተሉ ይችላሉ::

ለምሳሌ በኔዘርላንድ የሕግ ሥርዓት ውስጥ፤ የፀደቀ ዓለም አቀፍ ስምምነት ከሕገ መንግሥቱ የላቀ ቦታ አለው::[57] በተመሳሳይም በስዊስ ሕግ፤ ጠንካራ ድጋፍን በአገኘው አመለካከት መሠረት አንድ የፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ከስዊስ ሕገ መንግሥት ጋር የሚጋጭ ቢሆንም እንኳ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::[58] እንዲሁም እ.ኤ.አ. ጥቅምት 4 ቀን 1958 በተደነገገው የፈረንሳይ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 54 እና 55 እንደተመለከተው፤ ዓለም አቀፉ ስምምነት የፈረንሳይ ሕገ መንግሥታዊ ምክር ቤት

---

[54] ሮዛሊ ፒ. ሻፈር፥ የዓለም አቀፍ ሕግና የደቡብ አፍሪካ ሕግ የእርስ በርስ ግንኙነት፥ ጠቅላላ እይታ፥ ዓለም አቀፍና ኮምፓራቲቭ ሕግ ኳርተርሊ፥ ቅፅ 32፥ ክፍል 2፥ 1983፥ ገጽ 279::

[55] ፒ. ሲ. አይ. ጄ. ሲሪስ ኤቢ ቁጥር 44፥ ገጽ 24ን ይመልከቱ፤ እንዲሁም ፒ. ሲ. አይ. ጄ. ሲሪስ ኤ፥ ቁጥር 24 ገጽ 12ን ይመልከቱ::

[56] በደንዚንግ የፓላንድ ዜጎች ጉዳይ (1931)፥ ፒ.ሲ.አይ. ጄ. ሲሪስ ኤ፥ ቁጥር 1፥ ገጽ 307::

[57] ጆንኪር ኤች. ኤፍ. ቫን ፓርፕሪስ፥ የኔዘርላንድ ሕገ መንግሥትና የዓለም አቀፍ ሕግ፥ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ሕግ መፅሔት፥ ቅፅ 47፥ 1953፥ ገፅ 549-550፤ እንዲሁም የ1953ን የኔዘርላንድ ሕገ መንግሥትን አንቀጽ 65ና 66 ይመልከቱ::

[58] አርተር ሄፍሊገር፥ የሕገ መንግሥት መርሆዎች ደረጃ፥ የሰብዓዊ መብት በማስጠበቅ ረገድ ያለው ሥራ፥ የስዊዝ ዘገባ፥ የሰብዓዊ መብቶች መፅሔት፥ ቅጽ 13 ቁጥር 3፥ 1992፥ ገፅ 87::

በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ከተደረገ በኋላ ሊጸድቅ ይችላል::[59]

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከሕገ መንግሥት ጋር እኩል የሆነ ደረጃ የሚሰጥባቸው ሀገሮች አሉ:: ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ የፀደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከዩናይትድ ስቴትስ ሕገ መንግሥት ጋር በእኩል ደረጃ ይታያሉ::

የዩናይትድ ስቴትስ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 4 ፓራግራፍ 2 በዩናይትድ ስቴትስ ሥልጣን የተደረጉ ወይም የሚደረጉ ማናቸውም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከራሱ ከሕገ መንግሥቱና በሕገ መንግሥቱ መሠረት ከሚወጡ ሕጎች ጋር በአንድ ላይ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ መሆናቸውን ይደነግጋል:: በተመሳሳይም በ1948 በተደነገገው የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 122 ውስጥ እንደተመለከተው፣ የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ከሕገ መንግሥቱ ጋር እኩል ደረጃ የተሰጣቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ሌሎች ጥቂት ሀገሮች ለዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ከሕገ መንግሥቶቻቸው የበታች ደረጃን ይሰጣሉ:: በእነዚህ ሀገሮች ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በመቃረናቸው ምክንያት ተፈጻሚነት እንዲያገኙ አይደረግም:: ለምሳሌ በፖርቱጋልና [60] በግሪክ[61] ሕጎች ውስጥ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ከሕገ መንግሥት ያነሰ ደረጃ አላቸው::

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(4) መሠረት የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ስምምነቶች እንደማናቸውም ሌሎች ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው:: ቀደም ሲል እንደተመለከተው "ሕግ" የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የሚወጡትንም የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ያካትታል:: የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ በመሆኑም ማንኛውም ሕግ፥ የፀደቁ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትን ጨምሮ፥ ሕገ መንግሥቱን የሚቃረን ከሆነ የፀና አይሆንም:: አንድን ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በሚያፀድቅበት ጊዜ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስምምነቱ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱትን መርሆዎች የማይቃረን ስለመሆኑ ማንኛውንም ጥንቃቄ እንዲወስድ ይጠበቃል::[62] በመሆኑም፣ በኢትዮጵያ ሕግ የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ከሕገ መንግሥቱ የበታች ደረጃ አላቸው ብሎ መከራከር ይቻላል::[63]

---

[59] ለምሳሌ በፈረንሳይ የማስትሪች ስምምነትን መፅደቅ የተሰጠው ለፈረንሳይ የሕገ መንግሥት ፍርድ ቤት ሲሆን ይህም የሕገ መንግሥቱ መፅደቅ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ክለሳ ያስፈልገው እንደሆነ ለማረጋገጥ ነው::

[60] ኢሉየት ቫግኛ እና ኢቫሊን ሞንቴኖ፥ የአይቤሪያን ፔኒንሱላ፥ ስፔንና ፖርቱጋል፥ የአውሮፓ ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ስምምነት፥ 1992፥ ገፅ 175::

[61] ጆርጂያ ቤች ሊቫኑ፥ የአውሮፓ ሰብዓዊ መብት ጥበቃ የተደረገ ስምምነት፥ 1992፥ ገፅ 175::

[62] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፥ አንቀፅ 86(3)::

[63] በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 13(2) እንደተመለከተው ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕጎችና መርሆዎች ለትርጉም እንደመመሪያ በአገልግሎት ላይ መዋላቸው የሚሰጣቸው ቦታ ከሕገ መንግሥቱ የበለጠ ወይም ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ እኩል ሥፍራ ሊሆን ይገባል:: በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሕጎች የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ደንቦችና መርሆዎች የአንድ ሕግ ሥርዓት ሁለት ክፍሎች ናቸው ብሎ መከራከር ይቻላል:: እናም በሁለቱ የሕግ ሥርዓቶች መካከል ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ዓለም አቀፍ ሕግ እንደመመሪያ ስለሚያገለግል የበላይነት ይኖረዋል::

## ለ. የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና በብሔራዊ ሕግ አውጪ አካል የተደነገጉ ሕጎች

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት በአስፈጻሚው አካል ድርድር ተደርጎበት የተፈረመ አንድ ስምምነት ተገቢው እርምጃ ይወሰድበት ዘንድ በረቂቅ ሕግ መልክ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብለት ይደረጋል:: ምክር ቤቱ የቀረበለት ረቂቅ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ካገኘው ይህንኑ ረቂቅ ሊያፀድቀውና በአዋጅ መልክ እንዲደነገግ ሊያደርገው ይችላል:: በኢትዮጵያ ሕግ "አዋጅ"፣ ማለትም በተወካዮች ምክር ቤት የተደነገገ ሕግ፣ በደረጃው ከሕገ መንግሥቱ ቀጥሎ የሚገኝና አስፈጻሚው የመንግሥት አካል ከሚያወጣቸው ደንቦች የሚልቅ ነው::[64] ከዚህም ዕውነታ በመነሳት፥ ሕገ መንግሥቱ ከአዋጅ የላቀ ደረጃ እንዲሰጠው በተደረገባት ኢትዮጵያ፥ የፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚደነገግ አዋጅ ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ተሰጥቶታል በማለት መከራከር የሚያስኬድ ነው::

በፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና በአዋጅ መካከል ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ስምምነቱ ከአዋጅ የበላይነት ያለው ወይም የሌለው ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የሚናገረው ነገር የለም:: ሆኖም፣ በእነዚህ ሁለት ሕጎች መካከል ግጭት ሊፈጠር የሚችልባቸው ሁኔታዎች መከሰታቸው አይቀርም:: የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አቋም ምን መምሰል እንዳለበት አስተያየት ለመስጠት ከመሞከር በፊት በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና ተመሳሳይ ደረጃ በተሰጣቸው ብሔራዊ ሕጎች መካከል የሚከሰትን ግጭት ለማስታረቅ ሀገሮች የሚከተሏቸውን አቋሞች መመልከቱ ጠቃሚ ነው::

በአንድ በፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና በብሔራዊ ሕግ ወይም በአዋጅ መካከል የሚፈጠር ግጭትን ለማስታረቅ በስፋት ተቀባይነትን ያገኙ ሦስት አቋሞች ይገኛሉ:: የመጀመሪያው ከብሔራዊ ሕግ የላቀ ደረጃ ለስምምነት የሚሰጡ ሀገሮችን ይመለከታል:: ፈረንሳይ፥ ጣሊያን፥ ኔዘርላንድ፥ ሉግዘንበርግና ፓርቱጋል ይህንን አቋም ከሚከተሉ ሀገሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው:: እ.ኤ.አ. በ1946 የተደነገገው የፈረንሳይ ሕገ መንግሥት በዚህ አቅጣጫ የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰደ ሕገ መንግሥት ነው::[65] ይህም ልምድ እ.ኤ.አ. በ1958 ዓ.ም. በወጣው የፈረንሳይና በቀድሞዎቹ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት በነበሩ ሀገሮች ሕገ መንግሥቶች ተቀባይነትን አግኝቷል::[66] በዚህም መሠረት፣ የስምምነቱ ምንነት ከግምት ውስጥ ሳይገባና ከስምምነቱ በፊት ሆነ በኋላ የተደነገጉ ብሔራዊ ሕጎች እንዳይሰሩ ይደረጋል::

እ.ኤ.አ. በ1948 በተደነገገው የኢጣሊያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 10 ላይ የኢጣሊያ ሕግ ሥርዓት ሰፊ ዕውቅና ከአለው ዓለም አቀፍ ሕግ ጋር የተጣጣመ ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ተገልጿል:: በኔዘርላንድ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 94 መሠረት ደግሞ ከዓለም አቀፍ ስምምነት ጋር የተቃረኑ ሕጎች ተፈጻሚነት የላቸውም:: በሉግዘንበርግ፣ በብሔራዊ ሕግ ድንጋጌዎችና በዓለም አቀፍ ስምምነት መካከል ግጭት ሲፈጠር ዓለም አቀፍ

---

[64] የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያወጣው ሕግ በአዋጅ መደንገግ አለበት:: እንዲህ ያለው ሕግ ሕገ መንግሥቱን ሊቃረን አይገባም::

[65] የ1958 የፈረንሳይ ሕገ መንግሥት፥ አንቀፅ 55::

[66] ዴቪድ አር ዲነር፥ ገጽ 284::

ስምምነት የበላይነት ይኖረዋል::[67] በፖርቱጋል ሕግም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከብሔራዊ ሕጎች የላቀ ደረጃ አላቸው::[68]

ሁለተኛው አቋም፤ ከብሔራዊ ሕግ ጋር ተቃርኖ የተገኘ ዓለም አቀፍ ስምምነት ዝቅተኛ ደረጃ ሊሰጠው ይገባል የሚለውን የሚደግፍ አቋም ነው:: ይህ አቋም በብዙ ሀገሮች ተቀባይነት አግኝቷል። ለምሳሌ፤ በስዊድን የሕግ ሥርዓት ተቀባይነትን ያገኘ አሠራር የሚመስለው፤ ከስዊድን ሕግ ጋር ተቃርኖ የሚገኝ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ተፈጻሚነት ሊሰጠው አይገባም የሚለው ነው:: የኖርዌይ[69]፥ ካናዳና ቤልጂግ[70] ሕጎችም እንዲሁ ለዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ስምምነቶች ዝቅተኛ ደረጃ ይሰጣሉ::

ሦስተኛው አቋም፤ ለዓለም አቀፉ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና ለብሔራዊ ሕግ ተመሳሳይ ቦታ የሚሰጥ ነው:: በዚህም መሠረት፤ በእነዚህ ሁለት ሕጎች መካከል ግጭት ሲፈጠር ሁለቱ ሕጎች እኩል ደረጃ ኖሯቸው አንዱ ከሌላው ጋር የሚቃረን ከሆነ ኋላ የወጣው ቀደም ሲል ከተደነገገው ሕግ የበላይነት ይሰጠዋል የሚለው መርህ (ሌክስ ፓስቴሪዮሬ ዲሮጋ ፕሪዮሬ) ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል። ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን ሌሎች ህጎች በተመለከተ ግን ዓለም አቀፋዊ ሰብዓዊ መብት ስምምነት የበላይነት ይኖረዋል::

የኢትዮጵያን ሁኔታ በተመለከተ፥ ቀደም ሲል ለማተት እንደተሞከረው፥ የፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተደነገገ አዋጅ ጋር እኩል ደረጃ ተሰጥቶታል። በመሆኑም በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና በአዋጅ መካከል የተፈጠረ ግጭት እኩል ደረጃ በአላቸው ሁለት ብሔራዊ ሕጎች መካከል እንደተፈጠረ ግጭት ይቆጠራል:: ይሁን እንጂ፤ በስምምነትና በአዋጁ መካከል በሚፈጠር ግጭት የኤፌዲሪ ሕገ መንግሥት የትኛው ከየትኛው የበላይ ደረጃ ሊሰጠው እንደሚገባ ግልጽ መፍትሔ አይሰጥም::

እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም፤ ግጭቱን ከሚከተሉት ሁለት አማራጮች መካከል አንዱን በመጠቀም ለመፍታት ይቻላል:: የመጀመሪያው፤ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና በአዋጅ መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ለመፍታት ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ብሔራዊ ጥቅማችንን ይጎዳል ወይስ አይጎዳም በሚለው ጉዳይ ላይ በመመሥረት ነው:: ሁለተኛው፤ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና በአዋጅ መካከል ያለው ግጭት ኋላ የወጣው ሕግ ቀደም ሲል የወጣውን ሕግ ይሽራል የሚለውን መርህ መሠረት በማድረግ ለመፍታት ይቻላል::[71] ይህ መርህ የሚያመለክተው፤ የሀገር ሕግ አካል እንዲሆን የተደረገው ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ቀደም ሲል ከወጣ አዋጅ የላቀ ደረጃ እንደሚኖረው፤ እንዲሁም በአንጻሩ ኋላ የወጣ አዋጅ ቀደም ሲል ከፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት የላቀ ደረጃ እንደሚኖረው ነው::

የመጀመሪያውን ምርጫ በተመለከተ፤ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነትና በአዋጁ መካከል ያለውን ግጭት ለመወሰን ስምምነቱ የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚቃረን ወይም የማይቃረን ስለመሆኑ ማወቅ በእርግጥ አስፈላጊ ነው:: ይህም በኢትዮጵያ

---

[67] እንድሪው ዜድ ድሪዝቼውስኪ፥ ገፅ 132::

[68] አንቀፅ 19፥ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት ማንዋል፥ ገፅ 40::

[69] እንድሪው ዜድ ድርዝቼውስኪ፥ ገፅ 132::

[70] ዝኒ ከማሁ፥ ገፅ 64::

[71] ዊልያም ጄ. ራይስ፥ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በስዊዝ ሕግ ውስጥ ያላቸው ቦታ፥ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ሕግ መጽሔት፥ ቅፅ 46፥ 1952፥ ገፅ 647::

ጥቅሞች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን አንድ በአንድ መመርመርን ይጠይቃል:: በኤፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 86(2) እንደተመለከተው፣ በኢትዮጵያ የሚፈረም አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚያራምድ ሊሆን ይገባል:: የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 86(3) ዓለም አቀፍ ስምምነት የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅሞች እንዲጎለብት የሚያደርግ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ በፌዴራሉ መንግሥት ላይ ጥሏል:: በሌላ አነጋገር፣ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞቿን የሚጎዳ ማንኛውንም ዓለም አቀፍ ስምምነት አትፈርምም፣ አታጸድቅም:: በመሆኑም አንድ የተፈረመና የጸደቀ ዓለም አቀፍ ስምምነት ከጊዜ በኋላ ከተደነገገና የኢትዮጵያን ጥቅሞች ከሚያራምድ አዋጅ ጋር ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ አዋጁ ከዓለም አቀፋዊ ስምምነቱ የበላይነት ይኖረዋል:: የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 86(4) ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን የሚያስከብሩና የሕዝቦቿን ጥቅሞች የሚያራምዱ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ብቻ እንድታከብር ይጠይቃል:: ከዚህም በመነሳት በኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ አደጋ የሚያደርስ ማንኛውም የፀደቀ ዓለም አቀፍ ስምምነት ሊሰረዝ ይችላል:: ጉዳት የማያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ደግሞ ከአዋጁ የበላይነት ይኖራቸዋል በማለት መከራከር ይቻላል::

ሁለተኛው አማራጭ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ፣ የፀደቀ ዓለም አቀፍ ስምምነት ሊሰረዝ የሚችለው ኋላ ከተደነገገ አዋጅ ጋር ብቻ ተቃርኖ ከተገኘ ነው:: ይህንንም አቋም መከተል ኢትዮጵያን በእርግጥ "በይዘቱ በጣም አጠቃላይነት ላለውና ግልጽ ላልሆነ ዓለም አቀፍ ሕግ" የበላይነት መስጠትን በጥርጣሬ ከሚመለከቱት የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ቡድን ውስጥ እንድትካተት ያደርጋታል:: ይህንን አማራጭ ተከታይ የሆኑ ሀገሮች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚመለከቷቸው፣ የመዋዠቅ ጠባይ ያላቸው፣ የኃያላን ሀገሮችን ጥቅሞች በሚያስከብሩበት ደረጃ የእነሱን ጥቅሞች በትክክል ለማስከበር የማይችሉ መርሆዎች ስብስብ አድርገው ነው:: ሀገሮች ይህን አማራጭ ሊከተሉ የሚችሉበት ምክንያት ለዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሁለተኛ ደረጃ ለመስጠት በመፈለግ ነው:: በመሆኑም ኋላ የተደነገጉ ሕጎች ቀደም ሲል ከተደነገጉ ሰብዓዊ መብት ሕጎች የበላይነት አላቸው የሚለውን መርህ በመቀበል ኋላ ከተደነገገና በእኩል ደረጃ ላይ ከሚገኝ ሕግ ጋር ተቃርኖ የሚገኝ ዓለም አቀፍ ስምምነትን ለመሻር እንደምክንያት ይጠቀሙበታል::

ይሁን እንጂ፣ አንድ ብሔራዊ ሕግ ወይም አዋጅ ቀደም ሲል ከጸደቀ ዓለም አቀፋዊ ሰብዓዊ መብት ስምምነት የበላይነት እንዲኖረው ለማድረግ በማሰብ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት አማራጮች መካከል አንዱን ወይም ሌላውን ፍጹም በሆነ መልኩ መጠቀም አንድ ሀገር የገባችውን ዓለም አቀፋዊ ግዴታዎች በእርግጥ ዋጋ ሊያሳጣቸው ይችላል:: ያለጥርጥርም እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ሀገሮች ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን እንዲያከብሩ የሚያስገድዱትን የቬና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረታዊ መርሆዎች የሚቃረን ነው:: በዚሁ የቬና ስምምነት መሠረት አንድ ሀገር የዓለም አቀፍ ስምምነት አካል የሚሆነው ፈቃደኛ ከሆነ ብቻ ነው:: ይኸው ሀገር አንድን ስምምነት ከአፀደቀ ግን በስምምነቱ የተጣሉበትን ግዴታዎች በቅን ልቡና ማሟላት ይጠበቅበታል::[72] በልዩ ሁኔታዎች ምክንያት ካልሆነ በስተቀርም በስምምነቱ መሠረት የገባባቸውን ግዴታዎች ላለማክበር የብሔራዊ ሕጎቹን ድንጋጌዎች እንደ ምክንያት መጥቀስ አይችልም::[73]

በዚህ ጸሐፊ አስተሳሰብም የፀደቀ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት ከአዋጅ አንፃር በኢትዮጵያ ያለውን ደረጃ ለመወሰን ከላይ የተመለከቱትን ሁለት አማራጮች በጋራ ተፈጻሚ ማድረግ ይቻላል:: ይሁን እንጂ፣ ሁለተኛው አማራጭ የመጀመሪያውን አማራጭ በሚቃረን መልኩ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም:: እንደሚታወቀው፣ የፀደቀ

---

[72] የ1969 የቬየና የዓለም አቀፍ ስምምነት፥ አንቀፅ 26::

[73] ዝኒ ከማሁ፥ አንቀፅ 46 እና 47::

ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ልዩ ዓይነት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ናቸው:: እነዚህም ኢትዮጵያ አካል የሆነችበት የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ የጋራ አመለካከቶችንና ጥቅሞችን የሚወክለው የልማዳዊው ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሕግ ድጋፍ ያላቸው ናቸው:: እ.ኤ.አ. በ1948 በተደነገገው በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ድንጋጌና በሌሎች ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ድንጋጌዎችና መርሆዎች ተመሳሳይ ባሕሪ ኖሯቸው ወደ ኋላ በሚዳብሩ አጠቃላይ የዓለም አቀፍ ሕግ ድንጋጌዎች ብቻ ካልሆነ በስተቀር በሀገሮች ሊጣሱ የማይችሉ ቋሚ ባሕሪ ያላቸው (jus cogens) መርሆዎች ናቸው::[74]

ዓለም አቀፍ ሕግ፣ መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችንና መርሆዎችን ሁልጊዜ እንዲያከብሩ ይጠይቃል:: የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 13(2)ን መጥቀስ ይህንን ክርክር የሚያጠናክር ነው:: ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተረጋገጡት መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ድንጋጌ፥ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብትና ሰብዓዊነት ስምምነቶችና መርሆዎች አኳያ፥ ሊተረጎሙ እንደሚገባ በግልጽ ያሳያል:: ይህም ሁኔታ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ያላቸውን በጣም ወሳኝ ደረጃ የሚያረጋግጥ ነው::

በመሆኑም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ሁሉ የኢትዮጵያን ጥቅሞች ሊያራምዱ የሚችሉ የድንጋጌዎችና መርሆዎች ስብስቦች ሆነው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው:: እንደዚህ ያሉ ስምምነቶች ኋላ ከተደነገጉ አዋጆች ጋር የተቃረኑ ሆነው መገኘታቸው የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ለማስከበር ቃል የገባለትን የኢትዮጵያን ጥቅሞች ይጎዳሉ የሚል አንድምታ አያሰጥም:: ነገሩ እንደዚህ ከሆነ፣ ኋላ የተደነገገ ሕግ ቀደም ሲል የነበረን ሕግ ይጥሳል የሚለውን መርህ ምክንያት በማድረግ ኋላ ከወጡ አዋጆች ጋር ተቃርነው የሚገኙ የፀደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሻር፥ ማሻሻልና ለጊዜው ከመተግበር እንዲቆሙ ማድረግ የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚጎዳና እንዲሁም የዓለም አቀፍ ሕግን የሚጻረር ነው:: ሆኖም፣ በተቃራኒው፣ ቀደም ሲል የተደነገጉ አዋጆችን ኋላ በፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ምክንያት ለመሻር፥ ለማሻሻልና ለጊዜው ከመተግበር ማቆም ይቻል ዘንድ ይህንኑ መርህ እንደ መሠረት መጥቀስ ይቻላል::

## መደምደሚያ

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ልዩ ዓይነት ስምምነቶች ናቸው:: በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረትና በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(4) በግልጽ እንደተደነገገው የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የሕገ መንግሥቱን መስፈርቶች አሟልተው እስከተገኙ ድረስ በኢትዮጵያ ላይ ዓለም አቀፍ አስገዳጅነት አላቸው:: ነገር ግን እንደዚህ ያሉ ስምምነቶች በሀገሪቱ ውስጥ ተፈፃሚነትን እንዲያገኙ በሕትመት ተዘጋጅተው መውጣታቸው አስፈላጊ ነው::

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ያፀደቀችው ለዜጎቿ ጥቅም ስትል ነው:: በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝቦች እነዚህ ስምምነቶች ስለመኖራቸው የማወቅ መብት አላቸው:: ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው ስምምነቶቹ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ሲወጡ ነው:: በዚህ መሠረት፣ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 71(2) የአገሪቱ ርዕሰ

[74] ዲተር ግሌክ፥ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግን በሥራ ላይ ስለማዋል፥ ችግሮችና ቅድሚያዎች፥ ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ሪቪው፥ ቁጥር 281፥ ከመጋቢት እስከ ሚያዝያ 1991፥ ገፅ 141::

ብሔር እነዚህን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን እንዲያሳትሙ ሲደነግግ እንዲሁም ደግሞ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 5(ሀ) እነዚህ የፀደቁ ስምምነቶች በሀገሪቱ ውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ሕትመት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊቆጠር እንደሚገባው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የፀደቁትን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን በሙሉ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት፤ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነት በአንድ መንግሥት መፅደቅ ማለት ያ መንግሥት ራሱን ለዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አስገዝቶ ለስምምነቱ እንደቆመ ያመለክታል፡፡ "በቃል መታሠር" የሚለው አባባል፥ በቪየና ስምምነት አንቀጽ 26 እንደሰፈረው፥ አንድ ሀገር ግዴታውን ለመወጣት ስምምነት በሚያደርግበት ወቅት በቅን ልቦና ግዴታውን እንደሚወጣ ያመለክታል፡፡ ይህ መርህ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮች ለፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በተለያዩ ሕጎቻቸው ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዲሰጡ ይጠይቃል፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 9(4) እንደሚያመለክተው፤ ሕገ መንግሥት የሕጎች ሁሉ የበላይ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ ሰፍሯል፡፡ በዚህም መሠረት፤ የፀደቁ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች፥ እንደ ሌሎቹ ሕጎች ሁሉ፥ ለሕገ መንግሥቱ የበታች ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን፤ በእነዚህ ስምምነቶችና በሕገ መንግሥቱ የመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች መካከል ቅራኔ ሲፈጠር ሕገ መንግሥቱ የስምምነቶቹ የበላይ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊመራን አይገባም፡፡

የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 13(2) በሁለቱ ሕጎች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን አወዛጋቢ ሁኔታ ሊፈታው ይችላል፡፡ በአንቀጹ እንደሰፈረው፤ የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መተርጎም ያለባቸው የዓለም አቀፍም ሰብዓዊ መብት ድንጋጌን እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፋዊ ሰብዓዊ መብት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይህም በኢትዮጵያ የፀደቁ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ከሕገ መንግሥቱ ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ ቦታ ወይም ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ እኩል ሥፍራ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ ከፀደቁ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ጋር በእኩል ደረጃ ላይ የሚገኙ ሕጎችን በተመለከተ ደግሞ ማንኛውም አዋጅ፥ ከስምምነቶቹ በኋላ የወጣ እንኳን ቢሆን፥ እነዚህን ስምምነቶች የሚሽር፥ የሚያሻሽል ወይም ደግሞ ለጊዜው ከመተግበር የሚያቆም መሆን አይኖርበትም፡፡